# የጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር EB/EMAS/17/2015

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በአማራ ክልል በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋም ፈንድ ጽህፈት ቤት በተመደበ ገንዘብ በጦርነት ለተጎዱ ለሰቆጣ፣ ደሴ እና ከሚሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የዲጂታል ቤተ-መጻህፍት ማሽን አቅርቦት፣ ተከላና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. በዘመኑ የታደሰ ህጋዊና አግባብነት ያለው የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው፣
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
4. የዲጂታል ቤተ-መጻህፍት ማሽን አቅርቦት፣ ተከላና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች አይነትና ቴክኒካል የፍላጎት ዝርዝር መግለጫ (Specification) ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ቢሮ ቁጥር 103 ማግኘት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ /BID BOND/ ለሚያቀርቡት ጠቅላላ ዋጋ ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትእዛዝ (ሲ.ፒ.ኦ.) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል/በጥሬ ገንዘብ የሚቀርብ ዋስትና ገንዘቡ ለቢሮው ገቢ ተደርጎ የደረሰኙ ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር በፖስታ ታሽጎ የሚቀርብ ይሆናል
7. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሀሳቡን በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ ትምህርት ቢሮ በትምህርት ግብዓት ጥናትና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 103 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በሥራ ሰዓት ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 16 ቀናት ውስጥ ማስገባት የሚቻል ሲሆን በ16ኛው ቀን የጨረታ ሰነድ ማስገባት የሚቻለው እስከ ቀኑ 8፡00 ሰዓት ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡
8. ጨረታው የሚከፈተው ጨረታው አየር ላይ በዋለ በ16ኛው ቀን ሲሆን ካላንደር የሚዘጋው በዓል፣ ቅዳሜና እሁድ ቀን ከሆነ ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን የጨረታ ሳጥኑ 8:00 ሰዓት ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በትምህርት ቢሮ የስብሰባ አዳራሽ 8:30 ሰዓት ይከፈታል
9. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. በጨረታው መሳተፍ ለሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ቢሮ ቁጥር 103 ድረስ በአካል በመገኘት ወይም በፋክስ ቁጥር 0582201100 በመላክ ወይም በስልክ ቁጥር 0583205654. በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

# የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ